7ኛ ዓመት ቁጥር 3
7th Year NO.3

ሐረር ጥቅምት 1/1994
Harar October 11/2001

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| የአንዱ ዋጋ 1.00 ብር | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|

ማዉጫ

አዋጅ ቁጥር 28/1994
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 1994 የበጀት አመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ ቁጥር 28/1994 ........ ገጽ 256

## አዋጅ ቁጥር 28/1994 ዓ/ም

## በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1994 የበጀት አመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ::

ለ1994 የበጀት ዓመት በክልሉ ዉስጥ የሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገዉን በጀት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ አጽድቆ ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 52 አንቀጽ ንዑስ 2/ሠ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማጽደቅና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን የተሰጠዉ በመሆኑ፣

የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱን የ1994 በጀት ዓመት በጀት አጠቃሎ ማጽደቅና ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የሚከተለዉ ታዉጇል::

### ክፍል 1
### ጠቅላላ

1. ይህ አዋጅ የ1994 በጀት ዓመት በጀት አዋጅ ቁጥር 28/1994 ተብሉ ሊጠቀስ ይችላል::
2. ከሐምሌ 1/1993 ጀምሮ ሰኔ 30/1994 በሚፈጸመዉ በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ዉስጥ በክልሉ የሚገኘዉ ገቢ እና ከሌላ ገንዘብ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘዉ ሠንጠረዥ ዉስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሉ እንደተመለከተዉ፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. | ለመደበኛ ወጪዎች | ብር | 44,952,290.00 |
| ለ. | ለካፒታል ወጪዎች | ብር | 31,500,000.00 |
| ሐ. | መጠባበቂያ በጀት | ብር | 2,047,710.00 |
| | ድምር | ብር | 78,500,000.00 |

/ሰባ ስምንት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር/ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል::

3. ለፕሮፌሽናል ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንደዚሁም ለሥራ ማስኬጃ የተፈቀደዉ መደበኛ በጀት ወደ ደመወዝና አበል ማዛወር አይቻልም።
4. ለካፒታል በጀት ከተፈቀደዉ ወደ መደበኛ በጀት ማዛወር አይቻልም።
5. በየወሩ ሳይቋረጥ እየተከፈለ የሚያልቅ ሆኖ ለቋሚ የመንግስት ሠራተኞች አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች መመሪያ በማዉጣት የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ ለመስጠት፣ የክፍያዉንም ጊዜ ለመወሰንና በዚህ አኳኋን በሚሰጠዉ ብድር ላይ በዓመቱ 12 % ወለድ እንዲያስከፍል ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ክፍል 2
## የበጀት አስተዳደር

### 6. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አካላት ሥልጣን

ክልላዊ መንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየቢሮዎቻቸዉ ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደላቸዉን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፈል ታዟል።

1. ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየቢሮዎቻቸዉ ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደላቸዉን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል ታዟል።
2. የተፈቀደላቸዉ ጠቅላላ የበጀት መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ መንግስት ሥር ለሚተዳደሩ ሆስፒታሎች ባለፈዉ በጀት አመት ካስገኙት ትክክለኛ ገቢ 50% /ሃምሳ በመቶ/ ሳይበልጥ ከዘመኑ የበጀት አመት ገቢያቸዉ እንደአስፈላጊነቱ ወጪ እያደረጉ እንዲሰሩበት ለመፍቀድ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊዉ ሥልጣን ተሰጥቶታል።
3. የበጀት ዝዉዉር ሥልጣን ለሚከተሉት አካላት ተሰጥቶአል።

ሀ/ የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

1. በጀት ተፈቅዶለት በመከናወን ላይ ካለ የካፒታል በጀት በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ ካፒታል በጀት፣
2. መደበኛ በጀት ከፈቀደለት አርዕስት /ንዑስ አርዕስት በበጀት አመቱ መደበኛ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ አርዕስት /ንዑስ አርዕስት፡
3. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደዉ ወደ ካፒታል በጀት፣
4. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደዉ ደመወዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ፣

ለ/ ፋይናንስ ቢሮ

1. ከላይ በአንቀጽ 6/ሀ/ ከ1-4 ከተጠቀሰዉ በስተቀር፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ አካላት ሲጠይቁ፣ በአንዱ መደበኛ በጀት አርዕስት ዉስጥ ከአንድ ንዑስ አርዕስት ወደ ሌላዉ ንዑስ አርዕስት በየሂሳብ መደቡ፣
2. ጉዳዩ የሚመለከተዉ የክልሉ መንግስት አካልና የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሲስማሙበት በአንድ የክልሉ መንግስት አካል ሥር ለአንድ አርዕስት፣ ንዑስ አርዕስት፣ ፕሮጀክት በየሂሳብ መደቡ የተፈቀደን የካፒታል በጀት ወደ ሌላ አርዕስት፣ ንዑስ አርዕስት፣ ፕሮጀክት በየሂሳብ መደቡ፣
3. በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲፈቀድ በክልሉ በመደበኛ በጀት ዉስጥ ለመጠባበቂያ ከተያዘዉ ወደ ሌሎች ወጪዎች ፣
4. በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲፈቀድ ለክልሉ ለመደበኛም ሆነ ለካፒታል ወጪ ተፈቅዶ በሥራ ላይ ያልዋለዉን ተራፊ በጀት ወደ ሌሎች ወጪዎች፣

*ሐረር ጥቅምት 1 ቀን 1994 ዓ/ም*
*ፉአድ ኢብራሂም*
*የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት*
*ፕሬዝዳንት*

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 1994 የበጀት አመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ ቁጥር 28/1994 ........................................ገጽ 258

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
## የገቢ፣የዉጭ ዕርዳታና ብድር ማጠቃለያ

| | ብር | ብር |
|---|---|---|
| **ሀ/ መደበኛ ገቢ** | | |
| ቀጥታ ታክስ | 7,095,800.00 | |
| ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች | 2,233,200.00 | |
| ካፒታል ገቢ | | ------------- |
| የመደበኛ ገቢ ድምር | | 9,329,000.00 |
| **ለ/ የፌዴራል መንግስት ድጎማ** | | |
| ከግምጃ ቤት | 57,000,000.00 | |
| ከዉጭ ዕርዳታ | 4,611,000.00 | |
| ከዉጭ ብድር | 7,560,000.00 | |
| የድጎማ ድምር | | 69,171,000.00 |
| | | -------------- |
| ጠቅላላ ድምር | | 78,500,000.00 |

## በሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መንግሥት የ1994 በጀት አመት ወጪና የወጪ አሸፋፈን

1. ወጪ

ሀ/ መደበኛ ወጪ

| | | |
|---|---|---|
| አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ | ብር 13,289,240.00 | |
| ኢኮኖሚ አገልግሎት ዘርፍ | ብር 4,303,600.00 | |
| ማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ | ብር 27,359,450.00 | |
| መጠባበቂያ በጀት | ብር 2,047,710.00 | |
| የመደበኛ በጀት ድምር | | ብር 47,000,000.00 |

ለ/ ካፒታል ወጪ

| | | |
|---|---|---|
| ኢኮኖሚ አገልግሎት | ብር 12,123,350.00 | |
| ማህበራዊ አገልግሎት | ብር 17,662,950.00 | |
| ጠቅላላ አገልግሎት | ብር 1,713,700.00 | |
| የካፒታል በጀት ጠቅላላ ድምር | | ብር 31,500,000.00 |
| ጠቅላላ ወጪ ድምር | | ብር 78,500,000.00 |

2. የወጪ አሸፋፈን

ሀ/ የአገር ዉስጥ ገቢ

| | | |
|---|---|---|
| የታክስ ገቢ | ብር 7,095,800.00 | |
| ታክስ ያልሆነ ገቢ | ብር 2,233,200.00 | |
| የአገር ዉስጥ ገቢ ድምር | | ብር 9,329,000.00 |
| በጀት መረጃ | | ብር 57,000,000.00 |
| ጠቅላላ ገቢ | | ብር 66,329,000.00 |

ለ/ የዉጪ እርዳታ

| | | |
|---|---|---|
| የጥሬ ገንዘብ እርዳታ | ብር 4,611,000.00 | |
| የዉጪ እርዳታ ድምር | | ብር 4,611,000.00 |

ሐ/ የዉጪ ብድር

| | | |
|---|---|---|
| ከዉጪ ብድር | ብር 7,560,000.00 | |
| የብድር ድምር | | ብር 7,560,000.00 |
| የገቢ፣ የእርዳታና የብድር ጠቅላላ ድምር | | ብር 78,500,000.00 |